

CardinalCare
Virginia's Medicaid Program

# MEDICAID WORKS

## የፕሮግራም መምሪያ

### የVIRGINIA MEDICAID የሥራ ማበረታቻ ፕሮግራም ለአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች

VIRGINIA'S MEDICAID PROGRAM
DMAS

# MEDICAID WORKS
# የፕሮግራም መመሪያ

***MEDICAID WORKS*** በVirginia Medicaid በቅጥር ላይ ያሉ ወይም መቀጠር ለሚፈልጉ የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የቀረበ የሥራ ማበረታቻ ዕድል ነው። ***MEDICAID WORKS*** በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሲሆን የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰራተኞች የበለጠ ገቢ እንዲኖራቸው እና የበለጠ ቁጠባ ወይም ሀብት እንዲኖራቸው የሚያስችል፣ አብዛኛውን ጊዜ በMedicaid የሚፈቀድ የMedicaid ዕቅድ አማራጭ ነው። ይህ ፕሮግራም ሰዎች እንዲሰሩ፣ እንዲቆጥቡ እና የበለጠ ነፃነት እንዲያገኙ ቀጣይ የጤና እንክብካቤ ሽፋን ድጋፍ ይሰጣል። ለዚህ የMedicaid ፕሮግራም ለማመልከት፣ ግለሰቦች እነርሱ በሚኖሩበት ከተማ ወይም ካውንቲ ውስጥ ያሉ የማኅበራዊ አገልግሎቶች ክፍሎችን ማነጋገር አለባቸው።

**ለ MEDICAID WORKS** ፣ መስፈርቶችን ለማሟላት፣ አመልካቾች የገቢ መጠን፣ የሃብት መጠን የብቁነት መስፈርቶችን በአካባቢያቸው የማኅበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ ማረጋገጥ አለባቸው። ይኸም ማለት የአካል ጉዳተኛ ወይም አይነ ስውር የሆኑ ነባር እና አዲስ Medicaid ተሳታፊዎች፣ ጠቅላላ ተቆጣሪ ወርሃዊገቢያቸው ለግለሰብ ከ$1,732 ወይም ለጥንዶች ከ$2,351፣ እንዲሁም የሃብት መጠናቸው ለግለሰብ ከ$2,000 እና ለጥንዶች ከ$3,000 ያልበለጠ መሆን አለበት። በተጨማሪም አመልካቹ፦

- ✓ *መሆን አለበትቢያንስ 16 ዓመት ወይም ከ65 ዓመት በታች*
- ✓ ሥራ የተቀጠረ 2 ወይም ከቀጣሪ የተገኘና የቅጥር ቀኑ መቼ እንደሚጀምር የሚገልጽ ሰነድ ያለው፤
- ✓ የኮመንዌልዝ ነዋሪ የሆነ፤ እና
- ✓ የዩኤስ ዜጋ፣ የዩኤስ ዜጋ ወይም መስፈርቱን የሚያሟላ ኢ-ዜጋ

ለዚህ ፕሮግራም ዓላማ ሲባል፣ የደጋፊ ደህንነት ገቢ (Supplemental Security Income (SSI)) በሆነው በማኅበራዊ ደህንነት አስተዳደር (Social Security Administration (SSA)) ወይም የማኅበራዊ የአካል ጉዳተኝነት መድን (Social Disability Insurance (SSDI)) ፕሮግራሞች ውስጥ መሰተፍ የአካል ጉዳተኝነት መስፈርትን ያሟላል። የSSA የአካል ጉዳተኝነት ሰነድ የሌለው ማንኛውም ሌላ አመልካች፣ ብቁነቱ ከመወሰኑ በፊት፣ በግዛቱ የአካል ጉዳተኝነት ልየታ አገልግሎት (Disability Determination Services) ፕሮግራም መገምገም አለበት።

**በMEDICAID WORKS** *ውስጥ ለመሰተፍ፣ አመልካቾች ቀድመው በባንክ ወይም በሌላ የፋይናንስ አገልግሎት ተቋም ውስጥ የሥራ ማበረታቻ ሂሳብ (Work Incentive Account (WIN)) መፍጠር አለባቸው። የWIN መለያ በባንክ የሚገኝ ልዩ ሂሳብ አይደለም ነገር ግን ተመዝጋቢው ለዚህ አላማ የሚለይ መደበኛ የቼኪንግ ወይም የቁጠባ ሂሳብ ሊሆን ይችላል። የተገኘው ገቢ ብቻ በWIN መለያ ውስጥ ሊቀመጥ ይችላል። አንድ ወይም ከዚያ በላይ የWIN መለያዎች በተመዝጋቢዎች መሰየም እና የተገኘውን ገቢ በሙሉ ለማስቀመጥ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። የተገኘውን ገቢ በWIN መለያ ውስጥ በማስቀመጥ፣ ተመዝጋቢዎች እስከ $45,976 (ከጃንዋሪ 1፣ 2024 ጀምሮ) እና አመታዊ ገቢ እስከ $75,000 የሚደርስ ሃብት ሊኖራቸው ይችላል። ከላይ ባሉት የWIN መለያዎች ውስጥ በገንዘብ አጠቃቀም ላይ ምንም ገደቦች የሉም ስለዚህ እንደ አስፈላጊነቱ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። በሚከተሉት በIRS የተፈቀዱ መለያዎች ውስጥ የተቀመጡ መጠኖች ከዚህ ሃብት ጋር አይቆጠሩም፣ እንዲሁም ለፕሮግራሙ ብቁ መሆን ላይ ተጽዕኖ አይኖራቸውም። ይሁን እንጂ እነርሱም WIN ሂሳቦች ተብለው መታወቅ አለባቸው። እነዚህም የጡረታ ሂሳቦችን፣ የህክምና ቁጠባ ሂሳቦችን፣ የህክምና ተመላሽ ሂሳቦችን፣ የትምህርት ሂሳቦችን እና እራስን የመቻል ሂሳቦችን ያካትታል። እነዚህን ፈንዶች ማንቀሳቀስ የተከለከለ ነው።*

የሽፋን ተሳትፎ ሁሉም መስፈርቶች ከተሟሉበት ወር ቀጥሎ ባለው ወር የመጀመሪያ ቀን ይጀምራል። አንድ አመልካች ለወደፊት የስራ መጀመሪያ ቀን ካለው፣ የምዝገባ ጊዜው የሚፀናበት ቀን ከመጀመሪያው የስራ ቀን ቀደም ብሎ አይሆንም። ይሁን እንጂ፣ ቅጥር የሚጀምረው በወሩ የመጀመሪያ ቀን ካልሆነ በስተቀር፣ የፕሮግራም ተሳትፎ በቀጣዩ ወር የመጀመሪያ ቀን ይጀምራል።

**በMEDICAID WORKS** ውስጥ *ያለዎትን ተሳትፎ ለመቀጠል፣ ተሳታፊዎች የአካል ጉዳተኝነት ሁኔታቸው ያልተቀየረ፣ በቅጥር ላይ ያሉ፣ ከ65 ዓመት በታች የሆኑ፣ እንዲሁም ከላይ ከተጠቀሱት ገቢዎች እና ሃብቶች ያልበለጠ ሃብት ያላቸው መሆን አለባቸው። በተጨማሪም፣ ለተሳታፊው የደረሰ ከደመወዝ ውጭ የተገኘ ገቢ፣ በዚህ ሰነድ ውስጥ ከላይ እንደተጠቀሰው ከፌዴራል የድህነት ወለል 138% በታች ሆኖ መቆየት አለበት። ይሁን እንጂ፣ ተሳታፊው ወርሃዊ የSSDI ክፍያ የሚቀበል ከሆነ እና መጠኑ በሥራ እና/ወይም በኑሮ ውድነት ማስተካከያ (cost-of-living adjustment (COLA)) ጭማሪ ካሳየ፣ አዲሱ SSDI ክፍያ መጠን ከደመወዝ ውጭ የሚገኝ የገቢ ገደብ ከሆነው የፌዴራል የድህነት ወለል 138% ከበለጠ ተሳታፊው ይህን የጭማሪ መጠን ወደ WIN ሂሳብ ማስገባት አለበት።*

ብቁነት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ እንደገና ይገመገማል። ተሳታፊዎች፣ ሽፋናቸውን ሊቀይሩ የሚችሉ ለውጦች በሚኖሯቸው ጊዜ ለብቁነት ኃላፊያቸው ማሳወቅ አለባቸው፤ ይኽም የአድራሻ ለውጥ፣ የገቢ ለውጥ፣ የቅጥር ለውጥ፣ ወይም የቅጥር መቋረጥን የሚያካትት ሲሆን፣ በዚህ የሚወሰን አይደለም። የተሳታፊውን ቀጣሪ፣ የቅጥር ሁኔታ፣ የተገኘ ገቢ እና WIN ሂሳቦችን በተመለከተ በየጊዜው ሪፖርት ማድረግ ያስፈልጋል።

የደህንነት መጠበቂያ የፕሮግራሙ ክፍሎች በዘመም ወይም ሊቆጣጠሩት በማይችሉት ምክንያት ቅጥር ያቋረጡ ተሳታፊዎች የሥራ ቅጥር ሳይኖራቸው እስከ ስድስት ወራት በፕሮግራሙ ውስጥ እንዲቆዩ መፍቀድን ያካትታሉ። ተሳታፊው ያገኘው ከደመወዝ ያልተገኘ ገቢ ከፌዴራል የድህነት ወለል 138% የበለጠ መሆን አየለበትም። ለሥራ አጥ የሚሰጡ ክፍያዎች ከደመወዝ ያልተገኙ ገቢዎች እንደሆኑ ይቆጠራሉ። ይሁን እንጂ፣ አንድ ተሳታፊ ቅጥሩ ቢቋረጥ እና ከሥራ መቋረጥ መድን ገቢ ቢያገኝ፣ ተሳታፊው፣ ***ለMEDICAID WORKS*** *ብቁ እንደሆነ ለመቆየት፣ በእነዚህ የስድስት-ወራትየደህንነት መጠበቂያ ወይም "እፎይታ" ወቅት እነዚህን ሁሉንም ክፍያዎች WIN ሂሳብ ውስጥ ማስቀመጥ አለበት። ቅጥራቸውን ማስቀጠል ያልቻሉ እና ከፕሮግራሙ ማቋረጥ ያለባቸው ተሳታፊዎች በአካባቢው የማሕበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ በማናቸውም ሌላ የMedicaid ሽፋን ያላቸው ቡድኖች ውስጥ ለመሳተፍ መስፈርቱን ያሟሉ እንደሆነ በተፋጠነ ሂደት ግምገማ ይደረግላቸዋል። ይህ የሚጠናቀቀው ተመዝጋቢ ከፕሮግራሙ ከመቋረጡ በፊት ነው።*

**በMEDICAID WORKS** ውስጥ ከተሳተፉ በኋላ በWIN ሂሳቦች ውስጥ ካሉ የተሳታፊ ገቢዎች የተጠራቀሙና ከWIN ገደብ ያልበለጡ ሃብቶች በዚህ የብቁነት ልየት ውስጥ ግምት ውስጥ አይገቡም። በሌላ የMedicaid ሽፋን ያለው ቡድን ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ ሆነው ከተገኙ፣ ግለሰቡ፣ ቀጣይነት ያለው የMedicaid ብቁነት ውስጥ ከመቆጠራቸው በፊት እነዚህን ፈንዶች ለማስወገድ እስከ አንድ ዓመት ጊዜ ይኖረዋል።



*በ**MEDICAID WORKS** ውስጥ ከተሳተፉ በኋላ በሚከተሉት በIRS-የተፈቀዱ ሂሳቦች ውስጥ ከተቀመጡ የተሳታፊ ገቢዎች የተጠራቀሙና የWIN ሂሳቦች እንደሆኑ ከተሰየሙ ሂሳቦች ውስጥ የተጠራቀሙ ሃብቶች በማናቸውም የወደፊት የብቁነት ልየታ ውስጥ ግምት ውስጥ አይገቡም። እነዚህ በIRS የተፈቀደ ጡረታ፣ የህክምና ቁጠባ፣ የትምህርት እና የነጻነት መለያዎች ያካትታሉ።*

ለበለጠ መረጃ ወይም ለ***MEDICAID WORKS*** ለማመልከት፣ እባክዎ በሚኖሩበት ከተማ ወይም ካውንቲ ውስጥ ያለውን አካባቢያዊ የማሕበራዊ አገልግሎት መምሪያ ያነጋግሩ። የማግኛ መረጃ www.dss.virginia.gov/localagency ላይ ይገኛል።

## ማጣቀሻ ማስታወሻዎች፡-

1 "የአካል ጉዳተኛ" ማለት በማኅበራዊ ደህንነት አስተዳደር (Social Security Administration (SSA)) በተበየነው መሰረት በጤና እክል ምክንያት ሥራ መሥራት ያልቻለ ማለት ነው።

**2** *"የተቀጠረ" ወይም "በሥራ ላይ ያለ" ማለት አመልካች/ተሳታፊ በተቀናጀ ሁኔታ ውስጥ ተወዳዳሪነት ባለበት የሥራ ቅጥር ላይ መሳተፍ አለበት፣ እንዲሁም ከዝቅተኛ ምንዳ እኩል ወይም ከዚያ በላይ ደመወዝ የሚያገኝ ሆኖ እርሱም የደመወዝ ግብር የተከፈለበት መሆን አለበት (ማስረጃ ይያስፈልጋል)። በራስ የተቀጠረ ከሆነ፣ ገቢዎች IRS ማመልከቻዎች፣ የሩብ ኣመት ግምታዊ ግብሮች፣ በንግድ ሥራ መዝገቦች እና/ወይም በንግድ ዕቅድ ማስረጃ ሊቀርብላቸው የሚችሉ መሆን አለባቸው።*

ይህ ተቋም፣ በፕሮግራሞቹ እና በአገልግሎቶቹ፣ በዘር፣ በቀለም፣ በትውልድ አገር፣
በጾታ፣ በእድሜ፣ ወይም በአካል ጉዳት ላይ በመመስረት ልዩነት አያደርግም።



CardinalCare
Virginia's Medicaid Program

VIRGINIA'S MEDICAID PROGRAM
DMAS